# የጎንደር ደብረ ኀይል ወደብረ ጥበብ በአታ ለማርያም ካቴድራል ሰንበት ትምህርት ቤት

## የሐዋርያዊ አገልግሎት ትምህርት




**አዘጋጅ፡- በትረማርያም አበባው ካሣ**

**(የመጻሕፍተ ብሉያት፣የመጻሕፍተ ሊቃውንትና የመጻሕፍተ መነኰሳት ትርጓሜ መምህር)**


**ግንቦት ፲፬፣ ፳፻፲፰ ዓ.ም**

## ማውጫ

# ይዘት

**ሐዋርያዊ አገልግሎት** .......... 3
**የሐዋርያዊነት መሠረቶች** .......... 3
**ሐዋርያዊ ማን ነው?** .......... 3
**ሐዋርያውያን ልዑካን እነማን ናቸው** .......... 5
**ሐዋርያዊ ሊጠነቀቅባቸው የሚገቡ ጉዳዮች** .......... 5
**ፈተናዎች ከወዴት ሊመጡ ይችላሉ?** .......... 5
**ሐዋርያዊ የስብከት አገልግሎት ሊይዛቸው የሚገቡ ነገሮች** .......... 5
**ሐዋርያዊ የስብከት አገልግሎት መለያ ባሕርያት** .......... 6
**የሐዋርያዊ አገልጋይ መለያ ባሕርያት** .......... 6
**ሕዝብን ማወቅ** .......... 7
**የሐዋርያዊ ትምህርት አቀራረብ** .......... 7

# ሐዋርያዊ አገልግሎት

ሐዋርያት ከጌታችን ከመድኀኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ አግኝተው ያስተማሩት፣ በተግባር ያሳዩትና የኖሩት መልካም ምግባር ሁሉ ሐዋርያዊ አገልግሎት ይባላል። በዋናነት የሐዋርያት ዋና አገልግሎት የነበረው ስብከት ነው። ስብከት ማለት ኢአማንያን ወደ እምነት የሚቀርቡበት፣ አሕዛብ ወደ ሕዝብነት የሚቀየሩበት ክርስትና በዓለም ሁሉ የሚስፋፋበት መንገድ ነው። ቤተክርስቲያን ከምድረ እስራኤል ተነሥታ መላውን ዓለም እንድታዳርስ ስብከት ግንባር ቀደም የሆነ አስተዋጽኦ አበርክቷል። የስብከት አገልግሎት ዋና ተልእኮዎች፡-

- ✓ ያላመኑትን አስተምሮ ማሳመን
- ✓ ያመኑትን ማጽናትና መጠበቅ

ከጥንት ጀምሮ በተለያየ ዘመን የተነሡ ነቢያት፣ ካህናት፣ ሐዋርያት፣ ሊቃውንት ሕዝቡን አስተምረዋል። መልእክታትን በመጻፍና በመሳሰሉ ተግባራት አገልግለዋል።

# የሐዋርያዊነት መሠረቶች

**፩. በመንፈስ ቅዱስ መመራት፡-** ይህም ማለት የሐዋርያነት ሥራ የመንፈስ ቅዱስ እንጂ የሰው አለመሆኑን ማመን፣ ሊከበርበትና ሊመሰገንበት የሚገባው እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን ማመን ነው (የሐዋ. ሥራ 4፥9፣ ዮሐ.15፥5)።

**፪. መንፈሳዊነት፡-** አገልጋይ የመንፈስ ፍሬዎችን ገንዘብ ያደረገ መሆን ይገባዋል (2ኛ ጢሞ.3፥14)። ሐዋርያዊ አገልጋይ ራሱን የካደና ሰማዕትነትን ለመቀበል የቆረጠ መሆን ይገባዋል።

**፫. ትሕትናና ኀላፊነትን መወጣት፡-** እኔ አላገለግልም ብል የሚቀርብኝ እኔ እንጂ እግዚአብሔር አይደለም ብሎ ማሰብ ይገባል (ማቴ.3፥9)።

**፬. ጥበብ፡-** ሰዎችን እንዴት ማቅረብ እንደሚችል፣ ከባህሉ ጋር እንዴት መግባባት እንደሚችል፣ ጉባኤን እንዴት መመሥረት እንደሚችል...ወዘተ ልዩ ልዩ መንገዶችን ማወቅ አለበት። ምሳሌ እንደ ቅዱስ ጳውሎስ።

# ሐዋርያዊ ማን ነው?

በሐዋርያት ትምህርት አምኖ ሐዋርያዊ ክህነት፣ ሐዋርያዊ ትምህርት፣ ሐዋርያዊ ሃይማኖት፣ ሐዋርያዊ ምግባር ያለው ሁሉ ሐዋርያዊ ይባላል። በተጨማሪም አንድ ሰው ሐዋርያዊ የሚባለው የሚከተሉት ነገሮች ያሉት ወይም የሚከተሉት ነገሮችን የሆነ ነው።

**፩. በእግዚአብሔር የተጠራ፡** የእግዚአብሔር ጥሪ በሕልም፣ በራእይ፣ በሰው፣ በሥራ አጋጣሚ፣ ልብን በማነሣሣት፣ በትምህርት፣ በሥልጠና ወዘተ ይገለጣል። ሙሴና ዳዊት በእረኝነት ሳሉ፣ ኤልሳዕ በእርሻ እያለ፣ ጴጥሮስ ዓሣ ሲያጠምድ፣ ጳውሎስ ክርስቲያኖችን ሲያሳድድ፣ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ መጽሐፍ ሲያነብ በመንገድ ላይ ሳለ ተጠርተዋል።

**፪. ማገልገል ግዴታው መሆኑን የሚያውቅ፡-** ማገልገል መዳን የሚገኝበት መንፈሳዊ ሥራ ስለሆነ አማራጭ ሳይሆን ክርስቲያናዊ ግዴታ ነው (ማቴ.25፥14-30)።

**፫. አርቆ አሳቢነት ያለው፦** መንፈሳዊ አገልግሎት ከዘለዓለማዊው ሕይወት ጋር ጥብቅ ግንኙነት ያለው ስለሆነ ቅርብ ወራጅ መሆን አይገባም፡፡ ሐሳባችን ሥጋዊና ቅርብ ሳይሆን መንፈሳዊና ሩቅ መሆን ይገባዋል (ዮሐ.10፥16)፡፡

**፬. የትም ቢሆን ለመሄድ ዝግጁ የሆነ፡-** ሐዋርያዊ አገልግሎት ምቾትን፣ ድሎትን፣ ፍላጎትን፣ ቤት ንብረት መተውን ሊጠይቅ ይችላል፡፡ ይህ ደግሞ ሰማያዊ ዋጋ ያለው ነው፡፡

**፭. መንፈሳዊ ትጥቅን የታጠቀ፡-** ለዕውቀት የሚተጋ፣ በእምነትና በምግባር ጽናት የተመሰከረለት፣ በትዕግሥት ወደፊት የሚራመድ፣ መንፈሳዊ ብስለት ያለው፣ ካለፈው እየተማረ ስሕተቱን እያረመ ካለፈው የተሻለ ለመሥራት የጀማሪነት ችኩልነትን በአዋቂነት ዕርጋታ እያረመ የሚሄድ፣ እንደቃሉ የሚኖር፣ ለአገልግሎቱ አስፈላጊ የሆነውን ቋንቋ የሚያውቅ ሊሆን ይገባል (የሐዋ. ሥራ 2፥14)፡፡

**፮. ከፍርሀት ነጻ የሆነ፡-** ሐዋርያዊ መከራን፣ ችግርን፣ እሥራትን፣ ረኀብ ጥምን፣ እንግልትን፣ ማጣትን፣ መጠላትን የማይፈራና የማይሰቀቅ ሊሆን ይገባል፡፡ ፍረሀት የማንወደውን ሊያሠራን የምናምነውን ሊያስተወን ይችላልና፡፡ ስለዚህ መፍራት አይገባም (የሐዋ. ሥራ 18፥9)፡፡

**፯. ከኀፍረት ነጻ የሆነ፡-** ሐዋርያዊ ሰዎች በክፉ ቢነሡበት፣ አገልግሎቱን ቢያቃልሉበት፣ ቢንቁት፣ ቢገለልና ብቻውን ቢቀር እንኳ ያለኀፍረት ለወንጌል አገልግሎት መነሣት አለበት (ማር.8፥38፣ ሮሜ 1፥16፣ 2ኛ ጢሞ.1፥8-12)፡፡

**፰. ራስን ከማጽደቅ ስሜት ነጻ የሆነ ሊሆን ይገባል**

**፱. ከዘረኝነት፣ ከጠባብነት፣ ከወገናዊነት ነጻ የሆነ፡-** የሐዋርያዊ ትልቁ ዓላማ በወንጌል መረብነት ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ማስገባት ነውና ከዘረኝነት ነጻ በመሆን ተልእኮውን ከግብ ማድረስ አለበት (1ኛ ቆሮ.1፥8-11)፡፡ በሰው ልጅ እኩልነትና ነጻነት ያምናል እንጂ የሚወደውና የሚጠላው የሚያከብረውና የሚንቀው ዘር፣ ነገድ፣ ጎሣ፣ ሕዝብ፣ አካባቢ የለውም (ራእ.7፥9)፡፡

**፲. ኑሮዬ ይበቃኛል ማለትን የሚያውቅ**

**፲፩. ፍሬውን ወዲያው ካላየሁ የማይል፡-** የሐዋርያዊ አገልጋይ ድርሻ መዝረትና መኮትኮት ነው፡፡ ፍሬ እንዲያፈራ ማድረግ የእግዚአብሔር ድርሻ ነው፡፡

**፲፪. ለእያንዳንዱ ነፍስ የሚጨነቅ (ሉቃ.19፥1-9)**

**፲፫. ሕዝቡን የሚወድ ስለሕዝቡም ራሱን አሳልፎ የሚሰጥ (ዮሐ.10፥11)**

**፲፬. መስቀሉን በደስታ የሚሸከም (ማቴ.16፥24)**

በጠቅላላው ሐዋርያዊ ንጹሕ የሆነውን ወንጌል ከማስተላለፍ ውጭ በማያገባውና በማይመለከተው ነገር ውስጥ ገብቶ መዘላበድ የለበትም፡፡ ሐዋርያዊ አገልግሎቱ በፖለቲካ፣ በዘርና በግላዊ ጥቅም ሊተረጎምበት ይችላል፡፡ የእርሱ አገልግሎት ድካማችንን ያጋልጣል ብለው የሚፈሩ ባለሥልጣናት ሊቃወሙት ይችላሉ፡፡ ከሓድያን ሕዝቡን ያነሣሡበታል፡፡ ምእመናንም ሊጠራጠሩት ይችላሉ (የሐዋ. ሥራ 9፥26)፡፡ ይህ ሁሉ መስቀል ነውና በጽናት መጋደል ይገባዋል፡፡

## ሐዋርያውያን ልዑካን እነማን ናቸው

ማንኛውም ክርስቲያን በተለያየ መንገድ ሐዋርያዊ አገልግሎትን ያገለግላል። የአገልግሎት ዋጋን መሠረት ባደረገ መልኩ ሁለት ዓይነት ልዑካን አሉ። እነዚህም፡-

- ለሚያገለግል ዋጋው ይገባዋል በሚለው የጌታ ቃል መሠረት የዕለት ጉርሳቸውን የዓመት ልብሳቸውን ችለናቸው የሚያገለግሉን አገልጋዮች። ብዙ ጊዜ መደበኛ አገልጋዮች እየተባሉ ይጠራሉ (ማቴ.10፥10፣ ሉቃ.10፥7)
- የተለያዩ ሥራዎችን በመሥራት የራሳቸውን ወጭ ራሳቸው እየሸፈኑ የሚያገለግሉ አገልጋዮች ናቸው። ለምሳሌ ቅዱስ ጳውሎስ ድንኳን እየሰፋ ራሱን በራሱ እየረዳ ይኖር ነበር (የሐዋ. ሥራ 20፥33-35)።

የሐዋርያዊ ሥራ አካላት ብዙ ጊዜ መምህራን (2ኛ ቆሮ.1፥19)፣ አስተባባሪዎች (የሐዋ፣ ሥራ 6፥3)፣ በጎ አድራጊ ምእመናን (የሐዋ. ሥራ 12፥12) ናቸው። ሐዋርያዊ አገልግሎትን ከተመቻቹ አጋጣሚዎች፣ ከአንድ ሰው፣ ከሕፃናት፣ ከሚታወቁ ሰዎች መጀመር እንችላለን።

## ሐዋርያዊ ሊጠነቀቅባቸው የሚገቡ ጉዳዮች

- ከንቱ ውዳሴ (ሉቃ.17፥10)፡- ምንም ያህል ሥራው የተሳካና የተዋጣ ቢሆን ባለቤቱ እግዚአብሔር መሆኑን ማመንና መመስከር ይገባል። ዓላማችን ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር ማድረስ እንጂ እኛን የሚደንቁ ሰዎችን መሰብሰብ አይደለም።
- ዋጋ ከሌለው ሰማዕትነት መራቅ
- ጸጋን በገንዘብ ለማስተላለፍ ከመመኘት ወይም በሌላ አገላለጽ ከሲሞኒዝም መጠበቅ
- ተከታይ ከማፍራት (1ኛ ቆሮ.1፥12)፡- እስራኤላውያን አብርሃም አባት አለን እያሉ እየተመኩ ነገር ግን በአብርሃም ተስፋ አላመኑም ነበር። መምለክያነ ሰብእ መሆን አይገባንም።
- በራሳቸው የሚመኩ ክርስቲያኖችን ከማፍራት
- መከፋፈልን ከመፍጠር (የሐዋ. ሥራ 6፥1)

## ፈተናዎች ከወዴት ሊመጡ ይችላሉ?

- ከራሳችን (ድካም፣ መሰላቸት፣ አለመብሰል)
- ከባለሥልጣናት (የእነርሱን ሥልጣን የሚሻማቸው፣ ሕዝቡን የሚቀሰቅስባቸው ስለሚመስላቸው)
- ከወግ አጥባቂ ሽማግሌዎች
- ጥቅማቸው ከተነካባቸው ግለሰቦች (ጠንቋዮች፣ ባለዛሮች፣ ሌቦች/ የሐዋ. ሥራ 13፥4-8)።
- ልዩ ልዩ አመለካከት ካላቸው ሰዎች
- ከቤተሰቦቻችን/ከወዳጆቻችን

## ሐዋርያዊ የስብከት አገልግሎት ሊይዛቸው የሚገቡ ነገሮች

ሐዋርያዊ አገልግሎቶች የሚባሉት ስብከት፣ ዝማሬ፣ በጎ አድራጎትና የመሳሰሉት ናቸው። የቤተ ክርስቲያን ዋና ሐዋርያዊ አገልግሎቷ ስብከት ነው።

- የእግዚአብሔርን መሓሪነትና የሰውን ልጅ በደለኛነት ማሳየት
- የሰውን ልጅ ተስፋና የእግዚአብሔርን ይቅር ባይነት ማስረዳት
- ሰው በእግዚአብሔር ላይ እንዲተማመንና በሌሎች ላይ ለምሳሌ በገንዘብ፣ በሥልጣን፣ በዝና፣ በውበትና በመሳሰሉት እንዳይመካ ማሳወቅ፡፡
- የሰውን ልጅ ክቡርነት በመግለጽ በሥጋዊ ምኞቱ እንዳይገዛ ማስረዳት
- የመልካም ሥራን አስፈላጊነት በማሳየት ሰውን ለመልካም ሥራ ማነሣሣት
- መሠረታዊ ትምህርተ ሃይማኖትን በማስተማር ሰዎች ስለሃይማኖታቸው እንዲረዱ ማድረግ፡፡
- የትምህርቱን ዓላማ በግልጽ ማሳየት
- ነገረ ቅዱሳንን ማካተትና ከሚሰጠው ስብከት ጋር አጣጥሞ ማቅረብ መቻል አለበት
- የክርስትናን ግብ ማሳየት አለበት
- በምድራዊና ሰማያዊ ኑሮ መካከል ያለውን ዝምድናና ልዩነት ማሳየት አለበት
- ተገቢውን ትምህርት ለተገቢው ሰው፣ በተገቢው ጊዜ በተገቢው ቦታ መስጠት አለበት
- ችግሮችን የሚፈታ መሆን አለበት
- የሰባኪውን የግል ፍላጎት የሚያንጸባርቅ መሆን የለበትም
- ወገናዊ ያልሆነ አንድን የሕብረተ ሰብእ ክፍል ብቻ የማይጠቅስ መሆን አለበት
- ሥጋዊ ጥቅም የሌለበት ሊሆን ይገባል
- ሰዎችን ለማሞገስ ወይም ለመዝለፍ ተብሎ ያልተዘጋጀ መሆን አለበት

## ሐዋርያዊ የስብከት አገልግሎት መለያ ባሕርያት

- መጽሐፋዊ (መጽሐፍ ቅዱሳዊ፣ አዋልድ መጻሕፍት)
- ነገረ ሃይማኖታዊ (ምሥጢራተ ቤተክርስቲያንን፣ መሠረተ እምነትን፣ ቀኖና ቤተክርስቲያንን፣ ኦርቶዶክሳዊ ትውፊትን የሚገልጽ ሊሆን ይገባል)
- ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን የሚገልጽ
- የአባቶችን ትምህርት የሚጠቀም
- ማኅበራዊ ኑሮን የተመለከተ (ክርስቲያኖች በማኅበራዊ ሕይወት ድርሻቸውን መግለጽ፣ ክርስቲያናዊ የቤተሰብ አኗኗርን፣ የመነኰሳት አኗኗርን፣ ከሌላ እምነት ሰዎች ጋር እንዴት መኖር እንዳለባቸው የሚገልጽ መሆን ይገባዋል)፡፡

## የሐዋርያዊ አገልጋይ መለያ ባሕርያት

- ኦርቶዶክሳዊ እምነት ሊኖረው ይገባል
- የቤተክርስቲያንን ዶግማ፣ ቀኖና፣ ትውፊትና ታሪክ ማማቅ አለበት
- ሰው ሊገባው በሚችለው መልኩ መልእክቱን ማስተላለፍ አለበት
- በቂ ዝግጅት ማድረግ አለበት
- በመሚያስተምርበት ጊዜ አካላዊ እንቅስቃሴው፣ አለባበሱ፣ ድምፁና ሌላውም የተመጠነና የተስተካከለ መሆን ይገባዋል
- ዓላማውን መረዳት (የማንኛውም አገልጋይ ዓላማ ሰውን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ማስገባትና ራስንም ለመንግሥተ ሰማያት ማዘጋጀት ነው)
- አንባቢ መሆን አለበት
- በዘመኑ ያሉትን መረጃዎች በትክክል ማወቅ አለበት

- ከከንቱ ውዳሴ መሸሽ አለበት
- የሚያገለግለውን ሕዝብ ሥነ ልቡና ማወቅ ይገባዋል

## ሕዝብን ማወቅ

የሕዝቡን ሥነ ልቡና ወይም ማንነት ማወቅ ስንል ከማኅበራዊና ባህላዊ አኗኗር አንሥቶ እስከ ግለሰብ ሕይወት ያለውን የሕዝብ ፍላጎት፣ ችግር፣ ባህልና የመሳሰሉትን ጉዳዮች መረዳት ማለታችን ነው፡፡ ሕዝብን ማወቅ ጥቅሙ፡-

- ✓ የትምህርቱን ዓይነት ለመምረጥ
- ✓ የትምህርቱን ጥልቀት ለመወሰን
- ✓ የትምህርቱን ጊዜ ለመወሰን
- ✓ የትምህርቱን አቀራረብ ለመወሰን

አገልጋዩ የሕዝቡን የዕውቀት ደረጃ፣ ሥነ ልቡና (የሕፃናት፣ የወጣት፣ የአዋቂ፣ የድኻ፣ የሀብታም፣ የተማረ፣ ያልተማረ፣ የበሽተኛ፣ የጤናማ…ወዘተ ሥነ ልቡና ይለያያልና)፡፡ በሕዝቡ ያሉ ማሕበራዊ ተጽእኖዎችን፣ ኢኮኖሚያዊ ተጽእኖዎችን፣ ፖለቲካዊ ተጽእኖዎችንና ሃይማኖታዊ ዳራቸውን ማወቅ ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አገልጋዩ መጸለይ፣ ማንበብና ስለጉዳዩ ማስታዎሻ መያዝ፣ ከጉዳዩ ላለመውጣት ርእሱን መጠበቅ፣ ጉዳዩን ባሰበው ጊዜና ቦታ ማጠናቀቅ ይገባዋል፡፡ ተገልጋዩን ማኅበረሰብም በዕድሜ፣ በፆታ፣ በሥራ፣ በኑሮ ሁኔታ ከፋፍሎ ማገልገል ይገባል፡፡ ይህንን ማድረግ የሚከተሉት ጥቅሞች አሉት፡፡

- ➢ ያለውን ሀብት በትክክል ለመጠቀም ያመቻል
- ➢ ቦታን በትክክል ለመጠቀም ያስችላል
- ➢ ለክትትል ይጠቅማል
- ➢ የቡድን ሥራ ለመስጠት ይረዳል
- ➢ ለትምህርት ተከታታይነት ያመቻል
- ➢ ድግግሞሽን ያስቀራል
- ➢ የተመረጡ ትምህርቶችን ለተመረጡ ተማሪዎች ለማቅረብ ይረዳል
- ➢ ለግምገማ ያመቻል

ሐዋርያዊ በየትኛውም ቦታ፣ ጊዜና ሁኔታ ሊያገለግል ይችላል፡፡ በዋናነት የተለመዱ ቦታዎች ቤተክርስቲያን፣ ከሰርግ ቤት፣ ከኀዘን ቤት፣ በአደባባዮችና በመሳሰሉት ነው፡፡

## የሐዋርያዊ ትምህርት አቀራረብ

ሐዋርያዊ ትምህርት በተለያየ መልኩ ሊቀርብና ሊሰጥ ይችላል፡፡ የሁሉም አቀራረብ ዋና ዓላማ ክርስቶስ የገለጠውን እውነት ለሰው በሚሻለውና በሚረዳው መንገድ ለማቅረብ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ከተለመዱ የትምህርት አቀራረቦች መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡፡

- ነገረ ሃይማኖታዊ (Dogmatic)
- ታሪካዊ (Historical)
- ቅዳሴያዊ (liturgical)
- ሥዕላዊ (Pictural)

- ተውኔታዊ (Dramatic)
- ጉዞ (Tour and travel)
- ተግባራዊ (Practical)
- ውይይታዊ (Discussional/ panel discussion and group discussion)
- ውድድሮች
- ዐውደ ጥናት (ማስረጃ ማሰባሰብ፣ ማንበብ፣ ማየት፣ መጠየቅ፣ መተንተን፣ መተርጎም፣ ውሳኔ ላይ መድረስ)
- ዐውደ ርእይ (ኤግዚቢሽን)
- የልምድ ልውውጥ
- በጽሑፍ ማስተማር
- በድምፅና ምስል (Audio video) ማስተማር
- የርቀት ትምህርት (Distance education)
- የጥያቄና መልስ መርሐ ግብር
- ሴሚናር (Seminar)፡- በተለያዩ ሰዎች ስለአንድ ጉዳይ መረጃዎች የሚቀርቡበት መግለጫዎች ወይም ጽሑፎች የሚስተናገዱበት መርሐ ግብር ነው።